ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ታኅሣሥ 10 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# ሀገር አድን ትግሉ ከተዛባ ሀገር ማጣት ይከተላል

ታሕሣስ 10 2011

ሕዝብ የሚመጥነውን መንግሥት ያገኛል የሚለውን የምንቀበል ባይሆንም ላለው አገዛዝ በተወሰነ ደረጃ ቢሆን ሀላፊነት አለው ። ዛሬ እንደምናየው ባንዳን አርበኛ ፤ከሃዲን ታማኝ፤ወበጀለኛን ንጹህ ማለቱ ከተለመደ የሚከተለው ጉዳት በቀላሉ የሚወገድ አይሆንም ።የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለሀገራቸው ያበቃቸው አንዳድን ግለሠቦች ለምሳሌ ዕድሜ ለሹሙ ይኸው ነጻ ወጣን ሲሉ ማድመጥ ተገደናል ።ያሳዝናል ። ሹሙ ራሱም ከጉራ የተጣላ አይደለምና አንዱን ራሱን ያዋረደ ተለጣፊ ልሁን ባይ ይኸው ነጻ አውጣንህ ብሎ ተመጻድቆበታል። አጼ ኃይለሥላሴ ለባንዶች ቅድሚያ ሰጥተው እነ በላይ ዘለቀን ስለሰቀሉ በሀገራችን ከሃዲን የማክበሩ ባህል ተስፋፍቶብን መቆየቱ ይታወቃል ። የደርግ ነፍሰ ገዳዮችና የወያኔ ዘረኞች ዛሬ አንቱ ተብለው ይገኛሉ ። እነ ታምራት ላይኔ ዘርፈው አስገድለው ለራሳቸው ምሕረት ሰጠን፤ኢየሱስ ታየን ብለው ይኸው የክብር እንግዳ ሆነዋል ። 27 ዓመት ወይነው የከረሙት ከመቅጽበትም ዋና ነጻ አውጪ ተብለው እየተወደሱ ናቸው ። ትርኪ ምርኪ፤ዝብርቅርቅ። ታሪክን መርሳት፤ስህተትን መድገም ።

ሀገርም ይሄዳል ዜጋ ካልጠበቀው የተባለው እውነት ነው ። በነጻነት ሀገራችንን ያቆዩን የጥንቶቹ ከፍተኛ የደም ዋጋ ከፍለው ነው ። መስዋዕትነትን የፈራ ትውልድ ሀገሩን አይጠብቅም ። ሰነፍ ዜጋ የሚባለው ታሪኩን ረስቶ በመጣው ሁሉ የሚወናበደው ነው ። የሕዝብ ትግል ተደናቅፎና ተዛብቶ ባለበት ለውጥ መጣ ብሎ ቴ ቴ ከሞኝነት ያለፈ ሀገር ጎጂ ጥፋት መሆኑ ይታወቃል ።ሰዉ ተደናግሮ ትግሉን ካስረከበ ለሚከተለው ሁሉ ጉዳት ተጠያቂ መሆኑ አይቀርም ። ዛሬ በሀገራችን የሚፈነጩት ለህገር የታገከሉትና የሰተዉት ሳይሆኑ ሀገርን በትንሹም በትልቁም የጎዱ፤ከመጣው ባለነፍጥ ጋር የተወዳጁና የሰሩ ናቸው ። ስም ጥሩ የሚለን ሰው የሚኖር አይመስለንም ። ሁሉም አሁን ለያዙት ቦታና ላገኙት ነጻነት የሚበቁና የሚመጥኑ አይደሉም ። ወደ ቂሊንጦ መጓዝ ያለባቸው ናቸው ወደ ሹመት ያመሩት። በወያኔ ጉድጓድ እስር ቤቶች ሲሰቃዩ የከረሙትማ አሁንም በዚያው ናቸው--ያውም በሕይወት ካሉ ። ሹሙ ስለነሱ ሁኔታ ተጨባጭ መልስ መስጠት ከዝሆን ከብዶት ይገኛል ። ሀገርን በማሳፈር ላይ ካሉ ነፍሰ ገዳዮች ጋር ሲሞዳሞድ፤ ሲጠቃ ለባጀው ሕዝብ ይህ ነው የሚባል መክላከያ ሊሰ ጥ አልቻለም ። በሁኔታው የተበረታታው ወያኔ ድንበሬ አንገረብ ወንዝ ነው የሚል ሀሰትና ዕብሪትም እያሰማን ነው ። አማራን መናቅና ማጥቃት የሁሉም ዋና ተልዕኮ ሆኖ ስለቆየ ወያኔ እንደበፊቱ በሕዝብ ላይ ሊፈነጭ አስቧል--ግና የሚያስደነግጠውን እንደሚያገኝ ቃል ልንገባለት እንችላለን ። የትግላችን አቅጣጫ መቀየር ብቻ ሳይሆን ይዘቱ ስለተዳከመ ኢትዮጵያዊ ማንነቱ ራሱ ስለተካደ ፤ ከሽግግርና ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ ይልቅ ወያኔ ኢሕ አዴግን ማስቀጠል የሚል የክህደትና ሕዝብን ጎጂ ምርጫ ጉዞ ስለተያዘና ጠባቦች ነጻ መድረክ አግኝተው መፈንጨት በመቻላቸው ሀገራችን ለአደጋ ተጋልጣለች ። ይህን ሀቅ በመካድ ግን የኮለኔሉ ለውጥ መጣ ብለው ለግለሰቡም የድምቡሽት ጣኦት እየሰሩ የሚገኙ ወገኖች ግን ሀገርን እየታደጉ ሳይሆን እየጎዱ መሆናቸው ሊነገራቸው ይገባል ። ህገር ማዳን ዓይንን ከፍቶ ሀቅን አደጋውን አይቶና ተረድቶ ሀገርን መጠበቅን የግድ ይላል ።

ሀገር አድን ትግላችን--ማለትም የወያኔን ከፋፍለህ ግዛ ሰንሰለት በጥሶ፤የሕዝብን አንድነት አብስሮ የተካሄደው--ወያኔን ለቀውስ ዳርጎ የብሩህ ቀን ጮራን ፈንጠቅ ያደረገልንን ትግል ለማፈን በተለይ በአሜሪካ ሴራ በምስጢር ተሸርቦ፤ የዋሺንግተን ቅጥረኞች አማክረው ይህ ዛሬ የተሰየመው ሹም ታጭቶና ሰልጥኖ በቦታው ተሰየመ ። ሊያልቅለት የነበረው ወያኔ ጊዜን ገዛ ። መሸገ ። ለመመለስም የማሴር ጊዜ አገኘ ። ሹሙም ሊገድበው የነበረው ትግል አልታፈንም አለው -- ምንም እንኳን በርካታ አጨብጫቢዎችን ማግኘቱ ቢታይም ። ሀይማኖት ከፖለቲካ ደብለቅ ብሎም ለዚሁ ድጋፉ አንዱ ምክንያት  ነው ። ዋናው ፈተና ምን ዓይነት ስርዓትና መንግሥት የሚለው ሆኖ ተገኘ ። የሕዝብ ጎራ የሽግግር ሂደትና ሕዝባዊ መንግሥት--ወያኔ ኢሕአዴግ ይወገድ--የሚል ሲሆን ሹሙና ባዕዳንና ደጋፊዎቹ ግን የሽግግርን ሂደት ሰርዘው የነበረውን ያለውን ስርዓት ጠገን ደገፍ አድርገው ሊያስቀጥሉ መነሳታቸውን አስረገጡ ። የሽግግር ሂደት ሲሉ የነበሩት ቡድኖችም ከመቅጽበት በግል ጥቅም ተታለው ወያኔያዊውን ምርጫ፤ መንገድ፤ ደግፈው ሕዝብን ከዱ ። ይህን ሀቅ መቀበል  ግዴታቸው ነው ብንልም ስህተት አይሆንም ። የሕዝብን ፍላጎት እናከብራለን ካሉ በኋላ ተገልብጠው ይህን ፍላጎት የጣለውን ደግፎ መሰለፍ ሌላ ሊባል የሚችል አይደለም ። ይህ የሚመለከተው ራሳቸውን ኢትዮጵያዊ ለሚሉት እንጂ ጠባቦቹማ ባለው አገዛዝና ሁኔታ አልፎላቸዋልና ሌላ ሊጠብቁ ሊፈልጉ ማንም አይጠብቅም ። የዚህ ሁኔታ ውስጠየ ደግሞ ሹሙና አጋሮቹ የከፈቱት ህልውና የሰጡትን የጥበት ሰይጣን ሊቆጣጠሩ አለመቻላቸውን ይመለከታል ። ሀገር ገዢው ሹሙ ነው ወይስ ከ ፲ ያላነሱ ጠባብ ቡድኖች የሚለው ቁርጥ ያለ መልስን እስካሁን አላገኘም ። ባለ ሜንጫዎችም፤ግንጠላ ባዮቹም ሁሉ ማን ደፍሮን ብለው እየደነፉ ናቸው ። የፈለጋቸውን ወንጀል እየፈጸሙ ማንም ተቆጪ፤አሳሪ 'ቀጪ አላገኙም ። እንዲያውም ባለሜንጫዎቹና ጠባቦቹ የሚፈነጩት ታዳጊ ሹም ስላላቸው ነው ሲባል እየተደመጠ ነው ። በመሆኑም በርካታ ሰዎች የሹሞቹ ዕቅድና እውነተኛ አዋም ምን ይሆን በሚለው ላይ የሚያረካ ምላሽ ሊያገኙም ሊሰጡም አልቻሉም ። ከዚህ በተያያዘ መነሳት ያለበት አንድ አቢይ ጉዳይ ኢሕአፓን የሚመለከተው ነው ። ይህን ድርጅት ደርግም ወያኔም ጠላት ብለው ፈርጀው ያደረሱበት ጉዳት በሰፊው ይታወቃል ። ሁልቱም አውሬ አገዛዞችም የድርጅቱን ታሪክ በሰፊ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ ሲያጠለሹና ሲከልሱ መክረማቸውም የሚታወቅ ነው ። ስለ ድርጅቱ ቅንጣትም ዕውቀት ያለነበራቸው መስራች መስለው--አመራርም ነበርን እስከማለት ደርሰው--ልብ ወለዱን ታሪክ ብለው ቸብችበዋል ። አሁንም ቀጥሎ ያለ ነው ። ድርጅቱ ታሪኩን አስተካክሎ ለማቅረብ ቢጥርም በሚያስፈልገው ደረጃ ማስተባበሉ ራሱ ስራ በመሆኑና አሁንም በትግል ላይ ያለ በመሆኑ ችግር አለ ። ይህን ድርጅት የሹሞቹ አለቆች አይወዱትም ። ሁሉም ።ሻዕቢያ የድርጅቱ ጠላት ሆኖ የተገኘው ከዓመታት በፊት ነው ። አረቦቹ ደግሞ ድርጅቱ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ይጠሉታል ፡፤ አሜሪካም ከነጦር ሰፈሩ ከሀገራችን መሬት እንድወጣ ያደረገኝ ይህ ድርጅት ነው ብሎ ቂም ከመያዙ ባሻገር አሁንም በሀገራችን ጉዳይ ጣልቃ ገብነቱን ተቃዋሚ በመሆኑም ነው ።ኢሕ አፓ ቅኝ ገዢነትን በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ደረጃ መቃወሙንም ደብቆ አያውቅም ። አሜሪካ ወያኔን ደግፋና አቅፋ ያመጣችብንን መከራም አጋልጦና ተቃውሞ አውግዞ አቅዋሙን አስመዝግቧል ።በመሆኑም የሹሙን በስልጣን የመሰየሙንም ሴራ በጊዜ ድርጅቱ ያጋለጠ ከመሆኑም በላይ ህዝብ የትግሉን ግብ እንዳይለቅ በማሳሰብ የአሜሪካና የአረቦችንም ዕቅድ እንዲቃወም በመጥራት እንቅፋት ሆኖባቸው ይገኛል ። የጀመሩትንም ሂደት ሕዝብ ጎን ሆኖ ሊያደናቅፍ ይችላል ብለው ስለሰጉም ድርጅቱ እንዳይጠራ ብለው በመወሰናቸው ሁሉም ይምጣና ህጋዊ ይሁን ባዩ ሹም ይህን ጥሪ ኢሕአፓን የሚመለከት እንዳልሆነ ግልጽ አድርጓል ። እንዳያማህ ጥራው ነውናም ከድርጅቱ ወጥተው ወደ ፲ አመት ያሳለፉትንም በድርጅቱ ስም ጠርቶ እንዳይበላ ግፋው ነውና ውዳቂ አቀባበል እንዳደረገላቸውና ሊያነጋግራቸውም

እምቢ ብሎ መቆየቱንም ሕዝብ እያወቀው መጥቷል ። ሹሙና ደጋፊዎቹ በጅምላ ጸረ ኢሕአፓ ለመሆናቸው ምስክር መጥራት አያስፈልገንም ። የድርጅቱና የሕዝብንም ትግል ሊያንቋሽሹ ሲሞክሩ ታዝበናቸዋል ። የሀሰት ታሪክም በሚቆጣተሩት መገናኛ ብዙሃን አማካይነትም እያሰራጩ ናቸው ። የታፈኑ የድርጅቱ አባላትና መሪዎችም እስካሁን ደብ ዛቸው እንደጠፉም ነው ። ድርጅቱ ለዓመታት የታገላቸው ጠባቦችም በጠላትነት እንደፈረጁት መኖራቸው ምስጢር አይደለም ።

ሕዝብ የመጣበበት አገዛዝ የሚገባውና የሚመጥነው ነው እንዳይባልበት ለመብቱ ለሀገሩ የጀመረውን ትግል ማፋፋም አለበት ። በወያኔም በሱዳንም መሬቱን እየተነጠቀ ያለውን መቃወምና ማንነቱንና መሬቱን ማስከበር ይገባዋል ። ሀገር አድን ትግሉን በማፋፋም ይህ አገዛዝ የእኔ አይደለም ማለትም የግድ ይሆንበታል ። ተደናግሮና ተታሎ ስንት ደም የፈሰሰለትን ትግል ለአስመሳዮችና ተለጣፊዎች አሳልፎ መስጠት የለበትም ማለት ነው ። ሕዝባዊ መንግስት ምስረታ ነው ዋና ዓላማችን። የይስሙላ ተቃዋሚዎች ከግብግቡ ሳይደርሱ ወገቤን ብለው ለሹሙ ቢያሸረግዱ ይህ የሁሉም ስምሪት ሊሆን መጠበቅ የለበትም ። ለሕዝባዊ ግባችን፤ ትግላችንን ማፋፋምና ወያኔ ኢሕ አዴግን ማስወገድ መቻል አለብን ። ግባችንም ይህ ነው ። ያኔ ነው የራሳችን የምንለው ኢትዮጵያዊ መንግሥት በምርጫችን የሚሰየመው የሚቋቋመው ።

ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕ አዴግ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !!

ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል !!